### ፀሎት ስለዓለም ሰላም

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን።

የሰላም አብነት አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለቅዱሳን ሐዋርያትህ ሰላሜን እሰጣቹሃለሁ ብለህ እንደተናገርከው አሁንም እውነተኛውን ሰላምን አጥታ እየዋተተች ላለች ዓለማችን ሰላምህን ስጣት። የሰላም አባት ሆይ ጦርኞች በጦራቸው ባለፀጎች በሃብታቸው ሰላምን ሊያመጡ አይችሉምና

*ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ አይኖችህም መንገዴን ይውደዱ (ምሳሌ 23፡26)*

እውነታኝይቱን ሰላም ከአንተ እንድትሰጠን ዘንድ እንፀልያለን። ጌታ ሆይ የዓለም መንግስታት ሁሉ ለፍቅርህ እንዲገዙና በእውነተኛው የሰላም አባትነትህ እንዲጠቀሙ አድርጋቸው። የአንተ መንግስት የሰላም መንግስት ናትና ወደኛ ትምጣልን። በየእለቱ የሚነሳውን ጥልና ክርክር መለያየትና ደም መፋሰስን አጥፋልን።

ቸር አምላክ ሆይ በደምህ ለተመሰረተችው ቅድስት ቤተክርስትያን ሰላምና አንድነትን ስጣት። አገልጋዮችህንም የሰላም መልክተኞች እንዲሆኑ አድርግ። ሰው ሁሉ የአንዱ የአንተ አባታችን ልጅ ነውና በመተማመን በመቻቻልና በፍቅር ሰላምን



### በመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርት፤ ባህልና ታሪክ ኮሚቴ የሚዘጋጅ

ጌታሆይ የሰላምና የአንድነት አባት መሆንህን አውቀን ልመናችንን ወደአንተ ስናቀርብ በምህረትህ ስማን። አንተን ተስፋና ትምክህት አድርጋ እጅዋን ወደአንተ ለምተዘረጋልህ አገራችን ኢትዮጵያ ሰላምን ስጣት። አሜን።



መከነ ስላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን
አድራሻ፡ 8990 Grove street, Elk Grove, CA 95624
Tel (916) 690 8794
www.sacramentoselassie.com



# መልዕክተ መካነ ሥላሴ



ምእመናን ሆይ

ጥንታዊት የሆነች የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ለዘመናት በሃዋርያቶቹዋና በደቀመዛሙርቶች አማካይነት ከትውልድ ትውልድ በቃልና በመጻህፍቶቹዋ አማካይነት ለምእመናን መንፈሳዊ ትምህርት ስታስተምር ቆይታለች። ሆኖም ግን ለረጅም ዘመናት ቅዱሳን መጽሃፍቶች የሚጻፉት በቆዳ በተሰራ ብራና ላይና ከዱር እጽዋቶች ተቀምሞ በሚሰራ ቀለም ሲሆን፤ የሚጻፈውም በግእዝ ቋንቋ ነበር። በተለይም ደግሞ መጽሃፍቶች የሚባዙት በእጅ እየተጻፈ በመሆኑ የሚፈለገውን ያህል ተባዝቶ ለምእመናን የመሰራጨት አቅሙ በጣም ውሱን ነበር።

በዚህም ምክንያት ምእመናን በኢትዮጵያውያን አዋቂዎችና ሊቆች በተላያዩ ጊዜያት የተጻፉትን ቅዱሳን መጽሃፍቶች አንብቦና ተረድቶ ከመጽሃፍቶችም የሚገኙትን ቡራኬ ለመቋደስ አስቸጋሪ ነበር።

ሳክራሜንቶ መካነ ስላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤትክርስትያን በራሪ የትምሕርት ማስራጫ

ሆኖም ግን ለፈጣሪ ምስጋና ይግባውና በየቤተክርስትያኑና ገዳሙ የሚገኙ ካህናት፤ ዲያቆናት፤ መነኩሴዎች፤ ባህታውያንና ደብተራዎች ከትውልድ ትውልድ ትምህርቱን እያስተላለፉ እስከ ዛሬ ድረስ አቆይተውልናል።

በአሁኑ ዘመን ማተምያ ቤቶች በዝተው በሚግኙበት በዘመኑ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እነዚህን የእውቀትና ከአምላካችን ከእግዚአብሄር መገናኛ የሚሆኑንን ቅዱሳን መጽሓፍት ለምእመናን ማዳረስ በጣም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የሳክራሜንቶ መካነ ሰላሴ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን አቅሙና ችሎታው እስከፈቀደ ድረስ እምነታችንን የመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርትና የባህል ጥናት ኮሚቴ እያዘጋጀ በሚያቀርበው በራሪ መጽሄት ለማዳረስ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል። እያንዳዱም ምእመናን በመልዕክተ መካነ ሥላሴ አማካኝነት የሚቀርብለትን ቅዱስ ቃላቶችና የትምህርት ድርሰቶች ለሌሎች ላልደረሳቸው ኢትዮጵያውያን ማዳረስና ከትምህርቱ ማቋደስ ይገባዋል።

መልዕክተ መካነ ሥላሴ በየጊዜው ዋና ዋና የሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነቶችን በአጫጭር ጽሁፎች የምታቀርብ ተወዳጅ በራሪ መጽሄት እንደምትሆን ተስፋችን ነው።

*አንሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስጨረሰን ለፈጣርያችን ለመድሃኒታችን እግዚአብሔ ር ምስጋና ይግባው።*



## ምስጢረ ሥላሴ

ምስጢረ ሥላሴን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ዕምነት ተከታይ የሆነ ምእመናን በሙሉ ማወቅና መረዳት ያለበት ትምህርት ነው። የኢትዮጵያ መንፈሳዊ አባቶች በዚህ ምስጢር ለብዙ ዘመናት ሲወያዩበት የነበረ መሆኑን የታሪክ መጽሃፎች ያስረዳሉ። ለዚህም ሚስጢር ትርጉም የመጨረሻ እልባት ያገኘው በቅርቡ በአጼ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት በተደረገ መንፈሳዊ ጉባኤ እንደሆነ የታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ። ይህም የሚያሳየው የሥላሴ ምስጢር የእምነታችን መሰረት መሆኑና ከሌሎች ሃይማኖቶች የሚለየን ኦርቶዶክሳዊ ምልክታችን ነው። ስለዚህም ምስጢረ ሥላሴ ምን እንደሆነ ከዚህ በታች እናቀርባለን።

"በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መንፈሳዊ ትምህርት ምስጢረ ሥላሴ የማይታይና የማይመረምር ሁሉን ማድረግ የሚችል የሚታየውንም የማይታየውንም ፍጥረት ሁሉ የፈጠረ ይቅርታውና ቸርነቱ ያልተወሰነ ለዘለአለም የሚኖር መጀመርያውና መጨረሻው የማይታወቅ የማይመረመር አንድ አምላክ እንዳለ እናምናለን። እርሱም በአካላት ሶስት በመለኮት አንድ ነው። በሶስት አካላት አብ፤ ወልድ፤ መንፈስ ቅዱስ ይባላል። በመለኮት ግን አንድ ስለሆነ አንድ አምላክ ይባላል።



ስለዚህም ነው መንፈሳዊ አባቶች ሲያስተምሩ ፈጣርያችን ሥላሴ ናቸው ብለው የሚነግሩን። ሥላሴ አንድም ሶስትም ናቸው። ሶስትነታቸው በስም፤ በአካልና በግብር ነው። ለአብ ፍጹም አካል፤ ፍጽም ገጽ እንዲሁም ፍጹም መልክ አለው። ለወልድ ፍጹም አካል፤ ፍጽም ገጽ እንዲሁም ፍጹም መልክ፤ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፤ ፍጽም ገጽ እንዲሁም ፍጹም መልክ አለው።

በግብርም ሶስት ናቸው በመሆኑም አብ ወላጅ፤ ወልድ ተወላጅ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሰራጺ ናቸው። አብ የወልድ አባት በመሆኑ ይወልዳል እንጂ አይወለድም ወይም አያሰርጽም፤ ወልድም ልጅ በመሆኑ ይወለዳል ኢንጂ አይወልድም ወይም አይሰርጽም፤ መንፈስ ቅዱስም ሰራፂ ነው ኢንጂ አይወልድም ወይም አይወለድም።

የሥላሴዎች አንድነታቸው ደግሞ በባሕርይ፤ በሕልውና፤ በመለኮት፤ በልብ፤ በቃል፡ በእስትንፋስ በመሳሰሉት ነው።
እዚህ ላይ መጠንቀቅ ያለብን በስም በአካል በግብር ሶስት ናችው ካልን ሶስት የተለያየ አምላክ አለን ማለት አልመሆኑና አምላክ አንድ መሆኑን ነው። ሃይማኖት አበው እንደሚያስተምሩን አብም አምላክ ወልድም አምላክ መንፈስቅዱስም አምላክ ነው ግን አንድ ናቸው እንጂ ሶስት ናችው አይደሉም።"

እንግዲህ ሂዱና ኣህዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ እያስተማራቹህ ደቀመዝሙር አድርጋቸው (ማቴ . 28፡ 19-20)